# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች



# ጠቢቡ ንጉስ ሰሎሞን

ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Lazarus, Alastair Paterson

ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው): Ruth Klassen

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2024 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፥- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

ንጉስ ዳዊት ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ነው ፡፡ በእርሱ አገዛዝ ወቅት ፣ ከንጉስ ሳኦል የግዛት ዘመን ይልቅ አስር እጥፍ እስራኤል አስጋ ነበረ፡፡ አሁን ግን ከዚያ በላይ መግዛት አይችልም፡፡ ዳዊት አርጅቶ ነበረ ፤ ደክሞትም ነበረ! አሞትም ጭምር ! በምድር ያለው ሕይወቱ ወደ ሞት እየተቃረበ ነበረ፡፡





ከልጆቹ መካከል የሆነው
አዶኒያስ ለሰዎች እርሱ ንጉስ
እንደሚሆን ይነግራቸው ነበረ፡፡
ምንመ እንኳን የስሙ ትርጓሜ ፣
“የኔ ጌታ እግዚአብሔር ነው”
የሚል ቢሆንም አዶንያስ ግን
ጥሩ ሰው አልነበረም፡፡ ዳዊት
ራሱን ለመከላከል የማይችል
ደካማ መሆኑን በማወቅ ፣
ዙፋኑን ለመገልበጥ ይሞክር
ነበረ ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር
ሌላ ዕቅዶች ነበረው፡፡

የዳዊት ሚስት ቤርሳቤህ ልጇ ሰሎሞን
መንገስ እንዳለበት ታውቅ ነበር፡፡
የአዶኒያስንም ዕቅድ ለዳዊት ነገረችው፡፡
ታማሚ እንደነበረ ፣ ዳዊት መሪዎቹን
በአንድነት ሰብስቦ ሰሎሞንን በይፋ ንጉስ
አድርጎ ሾመው፡፡



የእስራኤል ሕዝብ ዳዊትን ያምነው ስለነበረ ፤ ሰሎሞን ከአዶኒያስጋ ብዙ ችግር አልነበረበትም፡፡ ዳዊት እግዚአብሔር የመረጠው ንጉስ ሰሎሞን መሆኑን ለእስራኤል ሕዝብ ነግሯቸው ነበረ፡፡ ከአጭር ጊዜም በኋላ ፣ ዳዊት ሞተ፡፡





ዳዊት ከመሞቱ አስቀድሞ ፣
ከሰሎሞንጋ እግዚአብሔርን
ስለመታዘዝና ጥሩ ንጉስ ስለመሆን
ከሰሎሞንጋ አውርቷል፡፡ ዳዊት ለልጁ
እንዲህ ብሎ ነገረው ፣ “በምትሰራው
ነገር ሁሉ እንዲሳካልህ ፣
በእግዚአብሔር መንገድ ሒድ ፡፡ ያም
ጥሩ ምክር ነበረ ! ሰሎሞንም በአባቱ
በዳዊት ዙፋን ላይ ተቀመጠ ፤
መንግስቱም ጸና፡፡

አንድ ሌሊት ሰሎሞን ሕልምን አለመ ፡፡ በሕልሙም ፤ እግዚአብሔር ተገለጠለትና እንዲህ አለው ፤ “ምን እንደምሰጥህ፤ ጠይቅ!” አንተ ምን ትጠይቅ ነበረ?



ሰሎሞን መልካም ንጉስ እንዲሆን ጥበብን ጠየቀ ፡፡ የወጣቱ ንጉስ ጥያቄ እግዚአብሔርን ደስ አሰኘው፡፡ ሰሎሞን የጠየቀውን ነገር አገኘ ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ራሱ ብዙ ሐብትና ክብርን ሰጠው፡፡



የሰሎሞንን ጥበብ ለማወቅ ሰዎች ብዙ ርቀት አልሔዱም ነበረ። አንድ ቀን ፣ አንድን ሕጻን ይዘው ሁለት ሴቶች መጡ። “የዚህች ሴት ልጅ ሕጻን በሌሊት ሞተ ፤ ከዚያም የሞተውን ልጅን በእኔ ሕያው ልጅ ቀየረችው።” ብላ አንዲቷ ሴት ተናገረች። “በፍጹም ! ሕያው የሆነው የእኔ ልጅ ነው ፤ የሞተው የእርሷ ልጅ ነው።” ብላ ሌላኛይቱ ተናገረች። ትክክለኛዋ እናት የትኛዋ እንደሆነች ፣ ንጉሱ እንዴት አውቆ መናገር ይችላል?

ከዚያም ንጉሱም እንዲህ አለ ፣ “ሰይፍ አምጡልኝ፡፡” እነርሱም ሰይፍን በንጉሱ ፊት ይዘው መጡ፡፡ በሰይፉ ምን ሊያደርጉ እንዳቀደ ምን ታስባለህ?



ንጉሱም አለ ፣ "ሕያው የሆነውን ልጅ ለሁለት ክፈሉትና አንደኛውን ለአንዱ አንደኛውን ለሌላው ስጡ፡፡" ሕያው የሆነውም ልጅ እናት የሆነችይቱ እንዲህ አለች፣ "አ! ጌታዬ ፣ ሕያው የሆነውን ልጅ ለእርሷ ስጣት ፣ ፈጽሞ አትግደላት፡፡"



ሌላኛይቱም እንዲህ አለች ፣ “ለእኔም
ለእርሷም አይሁን ፤ ክፈለው፡፡”





ንጉሡም እንዲህ አለ ፣ “ሕያው የሆነውን ልጅ ለመጀመሪያይቱ ስጣት፡፡ እርሷ ናት እናቱ፡፡”
ሁሉም የእስራኤል ሕዝብ ይሔንን ፍርድ ሰማ ፤ ንጉሡንም ሁሉ ሰው አከበረው፡፡ የእግዚአብሔር ጥበብ በእርሱ እንዳለም አስተዋሉ፡፡

የእስራኤልም ሕዝብ እግዚአብሔርን
ሚያመልክበት መቅደስ አልነበራቸውም፡፡
ዳዊትም ለመስራት ሲያቅድ ፤ እግዚአብሔር
እንዲህ አለው ፤”ልጅህ ለስሜ የሚሆን ቤት
ይሰራልኛል፡፡” ሰሎሞንም እጅግ አስደናቂ
የሆነ መቅደስን በኢየሩሳሌም ሰራ፡፡



መቅደሱንም ሰርቶ ለመጨረስ
ሰባት ረዥም ዘመንን ፈጀ፡፡
ነገር ግን ፣ ሰው ሁሉ ተሰብስቦ
፣ሰሎሞን መቅደሱን ሰርቶ
ለእግዚአብሔር የሚያቀርብበትና
ታላቅ ቀን መጣ፡፡



እጅግ አስደናቂ ከሆነ ጸሎት በኋላ ፣
ለሁለት ሳምንት የቆየ ንጉሱ እና
ሕዝቡ በሺዎች የሚቆጠሩ
መስዋዕቶችን የሚያቀርቡበት
ትልቅ በዓል አዘጋጁ።



ከዚህም በኋላ፣ እግዚአብሔር
ለሰሎሞን ተገልጦለት እግዚአብሔርን
እስካከበሩት ድረስ እርሱንና እስራኤልን
እንደሚባርክ ቃል ገባላቸው፡፡





በሚያሳዝን ሁኔታ ፣ ሰሎሞንም ሆነ የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን አልታዘዙትም ፡፡ ንጉሱ እግዚአብሔር እንዳያገቡአቸው የከለከላቸውን ብዙ ሴቶች አገባ፡፡ ሚስቶቹም ልቡን ወደ ጣኦታት አኮበለሉት፡፡ የአባቱ የዳዊት ልብ እንደነበረው ፣ ልቡም ለአምላኩ ለእግዚአብሔር ታማኝ አልነበረም፡፡



ሰሎሞን እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ያለውን ጊዜውን ሲያጠፋ ፣ ኢዮርብዓም
የሚባል አንድ ወዳጁ እንግዳ ልምድ ነበረው፡፡ አንድ ነብይም እግዚአብሔር
የሶሎሞንን መንግስት እንደሚከፍለውና ኢዮርብዓም በአስሩ ነገድ ላይ
እንደሚሰለጥን ነገረው፡፡ ኢዮርብዓምም በፍጥነት ወደ ግብጽ ምድር ሔደ
በዚያ ከቆየ ሰሎሞን ሊገድለው
እንደሚችል አውቆ ነበረና፡፡





በመጨረሻም ሰሎሞን ሞተ ፡፡
ልጁም ሮብዓም ሕዝቡ ላይ
እጅግ ብዙ ቀረጥን
ጣለባቸው፡፡ አስር ነገዶችም
አጉረመረሙ - ኢዮርብዓምም
መሪያቸው እንዲሆን መረጡ፡፡
የሰሎሞን ታላቁ መንግስትም
ለሁለት ተከፈለ፡፡ ልክ
የእግዚአብሔር ነብይ
እንደተናገረው ፡፡
እግዚአብሔር አለመታዘዝን
ሊባርክ አይችልም፡፡

ጠቢቡ ንጉስ ሰሎሞን

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

1ኛ ነገስት 1-12

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

መጨረሻ



60

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16